# የኢትዮጵያ ቀን ማህበር በስዊስ
# መተዳደሪያ ደንብ

## አንቀጽ 1፡ አጠቃላይ መግለጫ

1.1 የ «ኢትዮጵያ ቀን» በስዊስ ተብሎ የሚጠራው ማህበር ከ16 ጁላይ 2023 ጀምሮ በስዊዝ የሲቪል ሕግ (Art. 60 ff ZGB) መሠረት የተቋቋመ ሲሆን፣ መቀመጫውም በበርን ከተማ ይገኛል።

1.2 ማህበሩ ከፖለቲካዊ ፓርቲዎችና ከሃይማኖታዊ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ገለልተኛ ነው።

## አንቀጽ 2፡ ዓላማና ተግባር

2.1 በመላው ስዊዘርላንድ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን እና ትውልደ-ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች በየዓመቱ እየተገናኙ የሚያከብሩትን የጋራ በዓል ማዘጋጀት፣

2.2 የኮሚዩኒቲዎች የእርስ በእርስ ትውውቅ እንዲፋፋ ማቀራረብ፣

2.3 ሕጻናት የሀገራቸውን ባህልና መሰል እሴቶችን እያዩ እንዲያድጉ እድሎችን ማመቻቸት፣

2.4 በመካከላችን ያሉ ማንኛውም ዓይነት ልዩነቶቻችንን በእኩልነት እያየን በመከባበር የምንኖርበትን ባህል ማበልጸግ፣

2.5 የሀገራችንን ባህል እና ወግ ለስዊስ ዜጎች እያስገነዘብን በመካከላችን ሊኖር የሚገባውን ቅርርብ ማጠንከር፣

2.6 በአመት አንዴ ከምናካሂደው የበዓል ዝግጅት ከሚገኘው ገቢ 10 በመቶውን የእኛን ድጋፍ ለሚሹ ማህበራት ወይም ግለሰቦች መለገስ፣

## አንቀጽ 3፡ አባልነት

3.1 ዕድሚያቸው 18 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች፣ ቤተሰቦች፣ማህበራትና ድርጅቶች የማህበሩ አባል ሆነው ሊመዘገቡ ይችላሉ።

3.2 አባልነቱ በቦርዱ ውሳኔ የሚጸድቅ ይሆናል።

## አንቀጽ 4፡ የአባላት መማክርት ጉባኤ

4.1 የማህበሩ ከፍተኛ አካል የአባላት መማክርት ጉባኤ ነው።

4.2 የጉባኤው ስልጣንና ተግባሮች፡-

- 4.2.1 የፕሬዚዳንት/ትን እና የሌሎች የቦርድ አባላትን መምረጥና መሰናበት
- 4.2.2 የሂሳብ ተቆጣጣሪዎችን መምረጥ
- 4.2.3 ዓመታዊ ሪፖርትና የሂሳብ መግለጫ መቀበልና ማጽደቅ
- 4.2.4 በጀት ማጽደቅ
- 4.2.5 የአባልነት ክፍያ መጠን መወሰን
- 4.2.6 የመመሪያ ህጎች ለውጥ ማጽደቅ
- 4.2.7 በአባልነት መከልከል ወይም ማጥፋት ላይ የቀረቡ ቅሬታዎችን መወሰን

4.3 መደበኛ ዋና ጉባኤ በየዓመቱ አንድ ጊዜ ይካሄዳል።

4.4 ልዩ ጉባኤ በቦርዱ ወይም በአባላት ጥያቄ ሊጠራ ይችላል።

4.5 ግብዣ ከአጀንዳ ጋር ቢያንስ 3 ሳምንት በፊት ለአባላት መላክ አለበት።

4.6 የስብሰባ ፕሮቶኮል በጽሑፍ መዘጋጀት አለበት።

**አንቀጽ 5፡ ቦርድ (የአመራር ኮሚቴ)**

5.1 ቦርዱ ለ3 ዓመት ጊዜ የሚመረጡ 5 አባላትን ያቅፋል።
5.2 ሁሉም የቦርድ አባላት በስዊዘርላንድ ነዋሪ መሆን አለባቸው።
5.3 ማህበሩን በሕግ እና በአስተዳደር ወክሎ ዓላማዎቹን ይፈጽማል ያስፈጽማል
5.4 አዳዲስ አባላትን ይቀበላል
5.5 የምክክር ጉባዔ ያዘጋጃል
5.6 በቦርድ ደረጃ ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ማናቸውንም ጉዳዮች በኃላፊነት ያከናውናል።

**አንቀጽ 6፡ ፋይናንስ**

6.1 የማህበሩ ገቢ ምንጮች፡-
- 6.1.1 የአባልነት ክፍያ (በወር CHF 5)
- 6.1.2 ከዝግጅቶችና ፌስቲቫሎች የሚገኙ ገቢዎች
- 6.1.3 የመንግሥት ድጋፍ
- 6.1.4 ልገሳዎችና ውርሶች

6.2 የሂሳብ ዓመት ከካሌንደር ዓመት ጋር ተመሳሳይ ነው።

**አንቀጽ 7፡ ተጠያቂነትና የፊርማ ሥልጣን**

7.1 ለማህበሩ ግዴታዎች የሚጠየቀው የማህበሩ ንብረት ብቻ ሲሆን የግል ንብረት ተጠያቂነት የለም።
7.2 በቦርዱ የተመደቡ ኃላፊዎች (ፕሬዚዳንት/ት እና ጸሐፊው) ብቻ የሕጋዊ ፊርማ ሥልጣን ይኖራቸዋል።

**አንቀጽ 8፡ የቁጥጥር አካል**

የሂሳብ ሰነዶች ቁጥጥር ጉዳይ በአባላቱ ይፈጸማል።

**አንቀጽ 9፡ የአባልነት መቋረጥና መታገድ**

9.1 የማህበሩ አባል በማንኛውም ጊዜ አባልነቱን በጽሑፍ ሊያቋርጥ ይችላል።
9.2 እስከ ወሩ መጨረሻ ድረስ የአባልነት ክፍያ መክፈል ግዴታ ነው።
9.3 ቦርዱ የማህበሩን ጥቅም የሚጎዳ አባል ሊያግድ ይችላል።
9.4 የቅሬታ ሰሚ አካል የምክክር ጉባዔው ነው።

**አንቀጽ 10፡ የማህበሩ መፍረስ**

ማህበሩ ቢፈርስ፣ ትርፍና ካፒታሉ ተመሳሳይ ዓላማ ላላቸው ኢትዮጵያውያን ማህበረሰቦች ይተላለፋል።

...................................................
አውራሪስ ግርማ: ሊቀ መንበር

.............................................
አበበ ተሰማ: ጸሐፊ

...................................................
ሚሊዮን ላቀው: ሚዲያና የሕዝብ ግንኙነት

.............................................
የሻነህ አደፍርስ: የበዓል አዘጋጅ

.............................................
ሀዊ ሮት: የበዓል አዘጋጅ